ቤተ መንግስት መድረክ ላይ ዲዮንስዮስ ከባለቤቱ ጋር ተቀምጦ በመዝናናት ጊዜው አራት ሰዓት ገደማ በርቀት ከተማ ይታያል።

ዲዮንስዮስ፡- በድል አድራጊነት በጣም ተፈርቼ
ይኸው እኖራለሁ በኃይሌ ኮርቼ
ይህን የሰው ሀገር በጉልበት ገዝቼ
/መኳንንት ይገባሉ/
አሃ... የምመካባችሁ መጣችሁ ጀግኖቼ
አዳምጡኝ በእርጋታ ትዕዛዜን ልስጣችሁ
ጥፋተኛ ሲገኝ አምጡልኝ ይዛችሁ
ትዕዛዜን ለሚንቅ ህጌን ለሚንቅ ሰው
ፍርዱ የሞት ሲቃ ነው!

1 ኛ ሹም፡- ኧረ ያውም ሲያንሰው
እርሶ የያዙትን ህግና ሥርዓት
አጉድሎ የሚገኝ የሚገባው ነው ሞት
ኧረ እንዴት ያለ ነው የእርሶን ትልቅነት
ሳይረዳ ቀርቶ የሚሰራ ድፍረት

2 ኛ ሹም፡- ለእንዲህ ያለው ደፋር ለአመለ ቆሻሻው
የተሻለ ዘዴ ሞት ነው መጨረሻው
እንደሌለ አምናለሁ በዚህ ሰፊ ዓለም ላይ
እርሶ ያዘዙትን ደፍሮ አልፈጽምም ባይ!

/ዲዮንስዮስ እንዲቀመጡ ያዛቸውና ይቀመጣሉ
አንድ የዘበኛ ዓለቃ ይገባና እጅ በመንሳት.../

የዘብ አለቃ፡- ዲየንስዮስ ሆይ...
አንድ ቀባጣሪ አዕምሮውን ያጣ
ዛሬስ ብሎ ብሎ እግዜር ጉድ አመጣ
እሰው ሃገር ገብቶ ይህ ግፈኛ ጨካኝ
እንደምን ሞከረ ትዕዛዝ ሊሰጥ ሊዳኝ
እያለ ሲያወራ አግኝቼው በድንገት
እጀ እግሩን አስሬ በጠንካራ ብረት
ይዣው መጥቻለሁ ፍርዱን እንዲሰጡት

ዲዮንስዮስ፡- በሉ አሁን ሂዱና አምጡልኝ በፍጥነት
/መኳንንት እርስ በርሳቸው የመገረም ሁኔታ ይታይባቸዋል/

የዘብ አለቃ፡- እሺ... /ይወጣና በዘብ ይዞት ይመለሳል/
ዲዮንስዮስ፡- /በቁጣ/ በምን ምክንያት ነው ትዕዛዜን ጥሰህ
ይህን መጥፎ ወንጀል ሰርተህ የተገኘህ

ዳሞን፡- /በድፍረት/
በዕውነተኛ መንገድ ወንጀል አልሰራሁም

ግፈኛ ጫካኝ ነህ ብል አልተሳሳትኩም
ጥሩ ሃገር እያለህ መጥተህ ሀገሬ ላይ
እንዴት ማለት ደፊርክ ባለርስት ነኝ ባይ

ዲዮንስዮስ፡- /ይስቅና/
ኧረግ በጣሙን ይገርማል
ደፋር ሰው በዓለም ላይ አልፎ አልፎ ይገኛል
/ያስብና/
እንደዚህ ሊደፍረኝ እንደምን ሞከረ
ምንም አልፈርድበት ከሞት በስተቀረ
እንዲህ ያለ ድፍረት ማንም ሰው አይሰራ
/በእጁ እያመለከተ/
ወስደህ አርደህ ጣለው ስጋውን ለአሞራ

የዙብ አለቃ፡- እሺ ዲዮንስዮስ ሆይ ይህንን ደፋር ሰው
አሁን ወስጄ ነው ደሙን የማፈሰው!

ዳሞን፡- ዲዮንስዮስ ሆይ...
ጥያቄ ስላለኝ አድምጠኝ ለአንድ አፍታ
ከመሞቴ በፊት አንዴ ስጠኝ ፋታ
ሳትገምትብኝ ነገሩን በፍርሃት
ሚስትና ልጆቼን ሄጄ ልሰናበት

ዲዮንስዮስ፡- /ይስቃል.../
አያችሁት ይህንን ቀጣፊ አታላይ
ሞት ሲፈረድበት ሙት ልጆቹን ሊያይ
ተለቆ ለመሄድ አሁን መጠየቁ
ሞኝነቱ እኮ ነው ከዶ አለማወቁ
/ይስቃል.../
ልትሞት ስትቃረብ ልቀቁኝ ማለትህ
ለሰሚ ያስቃል በዝቶ ቂልነትህ

ዳሞን፡- ቂልነት አይደለም ብታስብ በመንፈስ
እቤቴ ደርሼ እስከመጣ ድረስ
ውድ ጓደኛ አለኝ ሆኖ የሚቆየኝ ዋስ

ዲዮንስዮስ፡- /በመገረም/
ይህ የሚገርም ነው ለአንተ ሲል የሚሞት
የሚዋስህ የለም እመነኝ በእውነት
ግን እንዳልከው ሆኖ የሚዋስ ካገኘህ
ፈቃዴ ነው እኔ ሄደህ ትመጣለህ
በል ዋስ የሚሆንህን በፍጥነት አስጠራ
መቼም አታገኝም

ለአራት ቀናት በፈቃድ ብትሄድ ግድ የለኝም…

/እጅ ነስቶ ይወጣል/

ዲዮንስዮስ፡- የማይሆንን ነገር ይሆናል የሚሉ
ብዙ ሞኝ ሰዎች በዓለም ይገኛሉ
ይህ የአሁኑ ሰው ሞት ሲፈረድበት
ሊፈፀም የማይችል ሃሳብ አደረበት
ዋስ ልፈልግ አለ ቢጨንቀው ቢጠበው…

1 ኛ ሹም፡- እንደዚህ ለማልቀስ ምንድን አጠገበው

2 ኛ ሹም፡- ይህ ሁሉ አለማሰብ እንዲያው ቀርቶ መና
መጨረሻው ሆነ ለቅሶና ልመና

/የዙብ አለቃ ጉብቶ እጅ ይነሳል/

የዙብ አለቃ፡- ዲዮንስዮስ ሆይ… እስረኛው ዋስ የሚሆነውን ልብ አስጠርቷል

ዲዮንስዮስ፡- መጠራቱስ ይሁን ለመሆኑ መጥቷል

የዙብ አለቃ፡- አዎ እደጅ ነው

ዲዮንስዮስ፡- ቶሎ የማታስገባው ታዲያ ለምንድነው

/እጅ ነስቶ ይወጣል እስረኛውን ያስገባል ቀጥሎም ዋሱ ይገባል/

ዳሞን፡- /ወደ ዋሱ እተመለከተ…/
ከልቤ የምወድህ ጓደኛዬ ፍቅሬ
በአደጋ ምክንያት በድንገት በታስሬ
ሞት ተፈርዶብኛል ምንም ተስፋ የለኝ
/ግን/ ሚስቴን እንድጠይቅ እባክህ ዋስ ሁነኝ

1 ኛ ሹም፡- አይ የልብ ጉጉት… ኧረ ለመሆኑ
እንዲዋሰው ይሆን አንዲህ መለመኑ

2 ኛ ሹም፡- አይ አንተ ደግሞ ጉዳዩን ሳታውቀው
ሁሉን ይሞክራል መቼም የጨነቀው
እንጂ በተረፈ ማን ለማን ይሞታል
መች ተደርጎስ ያውቃል መቼስ ይገመታል

1 ኛ ሹም፡- እኛ ምን ቸገረን በምኞት ቢሰክር
የማያገኘውን ለማግኘት ቢሞክር
ይልቅ እስቲ እንስማ ምን እንደሚል ያኛው

መቼም አይሞትለት ቢሆንም ጓደኛው
ምን ጊዜም አይድንም ፍረዱን ከመቀበል

2 ኛ ሹም፡- እኔ እኮ አላምንም እንዲህ ያለውን ቃል
ይህ ሰው ጓደኛውን ከራሱ በማብለጥ
ልሙትለት ያለው የሚያሰክር መጠጥ
ጠጥቶ ነው እንጂ በጤናውም አይደል

1 ኛ ሹም፡- ይህንን ጉድ ሰማን ጆሮ አይሰማው የለም
እጅ ነሳ ቀርቦ ምን ሊል ይሆን አሁን

ፒስያ፡- ዲዮንስዮስ ሆይ... በእርሱ ላይ ስለሰጡት ብይን
እኔ ዋስ ልሁነው ፈቃድዎ ይሁን
ወደ ሚስቱ ሄዶ ጠይቆ ይመለስ
ቢቀርም እኔ አለሁ እሞት ግዳጅ ድረስ
በማለት አነሆ እለምናለሁኝ

ዲዮንስዮስ፡- አንተ ከተዋስከው እኔ ምን ቸገረኝ
በል እስከ አራት ቀን ደርሰህ ለመመለስ
ስርሱ ዋስ ከሆነህ ቃልህን ሳታፈርስ
ልጅና ሚስትህን ቶሎ ተሰናብተህ
ያለህንም ሃብት ለምትሰጠው ሰጥተህ
ሰዓት ሳታሳልፍ እዚህ እንዳገኝህ
ነገር ግን ልብ አድርግ ሳትመጣ ከቀረህ
ሞት ይፈረድበታል ይህ ባልንጀራህ
.....
ይህ ልዩ ተአምር ነው አስደናቂ ሥራ
ለካስ ይፋቀራል እንዲህ ባልንጀራ
እስከዛሬ ድረስ እንዲህ ያለ መዋደድ
ፍፁም አላየሁም እኔ በሰዎች ዘንድ
ይህ ፍፁምነት ነው እውነተኛ ስሜት
እዩት ያሁኑን ሰው ስለፍቅር ሲሞት
ፈቃደኛ ሆኖ መሞቱን መረጠ
ምን ትርፍ አለው ለሰው ከዚህ የበለጠ
ያሁኖቹ ሰዎች ተግባር ይደር በልባችሁ
በጣም ጠቃሚ ነው ትምህርት ይሁናችሁ!

ትዕይንት **2**

ዲዮንስዮስ፡- በሃሳብ ተረብሼ መተከዜ ይብቃ
ተጫዋቾች ይምጡ እንስማ ሙዚቃ
/ሙዚቃ ይሰማሉ/

የዘብ አለቃ፡- ዲዮንስዮስ ሆይ
የሰጡት ውሰኔ ሰዓቱ ደረሰ
ዋስ ጠርቶ የሄደው ስላልተመለሰ
በደንቡ መሰረት ግብ እንዲያገኝ ፍርዱ
ወዶ የገባው ዋስ ይግባ በገመዱ

ዲዮንስዮስ፡- አሃ... ለካስ አንድ ሞኝ ሰው ተሰብኮ በወሬ
ቂል ሆኖ ከሞት ጋር ተቃጥሯል ለዛሬ

1 ኛ ሹም፡- እንዴት ሰው በሕይወቱ ሳያስብ በራሱ ይፈርዳል
ከራሱስ አብልጦ ሌላውን ይወዳል

ዲዮንስዮስ፡- ይህ ሰው በቁም ነገር ከሁሉም ቢበልጥም
ተወስኗልና ፍርዱ አይለወጥም
ውሳኔ ከሰጠሁ የለኝም ይቅርታ
አሁንም... በፍጥነት ወስዳችሁ እመግደያው ቦታ
የፍርዱ ትዕዛዝ ተነግሮ ለህዝቡ
አስፈላጊው ጉዳይ ይፈፀም በደንቡ!

የዘብ አለቃ፡- እሺ እንፈፅማለን ትዕዛዝዎን ሁሉ
በስርዓት አድርገን አሁን እርስዎ እንዳሉ

ዲዮንስዮስ፡- ደፋር ሰው ይመስላል ሳይ አረማመዱን
በሉ እስቲ እኛም ሄደን እናስፈጽም ፍርዱን
/ይወጣሉ/

ትዕይንት **3**

አልማዝ፡- ምነው ተረበሸ መንፈሴ ተቆጣ
ባሌ ሳይታሰብ ከቤቱ ከወጣ
ስምንት ቀን ሞላው መልእክትም አልላከ
ምን አገኘው ይሆን በምን ተማረከ
ግን እርግጠኛ ነኝ አይደለም በመቅበጥ
18 ዓመት አብረን ስንቀመጥ
አላየሁበትም አንዲተ እንኳን ጉድለት
ሆኖም ቀኝ ያውለው እግዚአብሔር ያስበለት
/ልጆች ይገባሉ/

ደፋሩ፡- እማማ ምነው አባበዬ እንደሄደ ቀረ

አልማዝ፡- እኔም በዚህ ጉዳይ አስቤ ነበረ

ግን ይዞት ይሆናል የሚያዘገይ ሥራ
ይመጣል አይቀርም ስለዚህ አትፍራ

ብርቱካን፡- ምነው ሆዴ ፈራ ምነው ሆዴ ባባ
ምን አግኝቶት ይሆን ይህን ጊዜ አባባ
እማማ አባክሽ ፈልጊው ሂጂና
ያለዚያው ምንጊዜም አላገኝም ጤና
በጤናው ባይሆን ነው እንጂ በተረፈ
ከመቶ የሚበልጥ ደብዳቤ ባልፃፈ
እስኪ ለደግ ያድርገው ፈጣሪ አምላካችን

አልማዝ፡- እንዴ...ምን ሆነሻል ምን ነካብኝ አንቺን
አባትሽ ከቤቱ እርቆ መሄዱ
እስኪደክመው ድረስ መውጣቱ መውረዱ
እኛን ሊደግፍ ነው ሊያኖረን በደስታ
አሁንም መሄዱ ራቅ ያለ ቦታ
ሊሰራ ብሎ ነው እንጂ ሚያሰጋ
ከቶ አይደርስበትም አንዳችም አደጋ
ይህ ሃሳብ ይቅርና ይልቅ ተቀመጡ
ምሳ እንድሰጣችሁ ደርሶ እንደሆን ወጡ
ወደ መድቤት ሂጀ መጣሁ ተመልሼ
/ትወጣለች/

ብርቱካን፡- እኔ አላውቅም እናጃ ሆዴ ተረበሸ
ደፋሩ፡- አይ... እትይዬ ለሊት ለሊት በህልሜ
አባባን አያለሁ ደግሜ ደግሜ
በጥፍሮቹ ቸዞት አንድ ዳልጋ አንበሳ
ሊበላው ፈልጎ በኃይል እያገሳ
ጥቂት ቆየት ብሎ ተለውጦ አንበሳው
ሰው ሆኖ ደግፎ አባባን ሊያነሳው
ይህንን አይና ከእንቅልፌ ስነቃ
እደነግጣለሁ መንፈሴ ተጨንቃ
ስለዚህ እባክሽ አንቺና እኔ ብቻ
አስፈላጊም ቢሆን እስከ ዓለም ዳርቻ
ሄደን እንፈልገው በምንችለው በኩል።

ብርቱካን፡- እሺ ምን ቸገረኝ ግን እስኪ አትቸኩል
ጉዳዩን እናጥና ከመረበሽ ፈንታ
/በር ይመታል/

ደፋሩ፡- እትዬ ቆይ እስኪ የውጭ በር ተመታ
/ሁለቱም ደ በሩ ይሮጣሉ ከአባታቸው ጋር ይገባሉ/

ብርቱካን፡- ስትቆይ ጊዜ ይህንን ያህል ቀን
ምን አገኘህ እያልን ተጠበን ተጨንቀን
ስለአንተ ስናስብ አየንህ በዓይናችን
እንግዲህ እንዳትሄድ ከመሃከላችን
ያላንተ ዕውሮች ነን ይደክማል ኑሮአችን
ደፋሩ፡- ምነው እንዲህ ቆየህ ይህን ያህል ጊዜ
ዳሞን፡- አይ እኔስ እንዲያው ነው የት ሄደች አልማዜ
ብርቱካን፡- ልሂድና ልጥራት እማዕድ ቤት ሄዳለች
ደፋሩ፡- እማማ ስላንት ብዙ ተጨንቃለች
/ልጆቹን ሲስም አልማዝ ትገባና ተቃቅፈው ከተሳሳሙ በኋላ/
አልማዝ፡- የሕይወቴ ፀጋ የኑሮዬ ጋሻ
የደስታ ምግቤ የችግሬ መርሻ
የተፈጥሮ ጓዴ ውድ ባለቤቴ
ወዳጄ ጌታዬ ወንድሜና አባቴ
ዛሬ መጥተህልኝ አንተን በማየቴ
ደስታ ሆነልኝ ጣፈጠኝ ሕይወቴ
ትካዜና ሃሳብ በደህና ሰንብቱ
ዘመዴ ጌታዬ ተመልሷል ቤቱ

ብርቱካን፡- የሕይወቴን ድጋፍ ካገኘሁ አባቴን
ደብተሮቼን ልያዝ ልጀምር ጥናቴን
በዓለም ላይ ደስ ብሎኝ መኖር የምመኘው
እንድታውቅ አባባ ካንተጋር ሆኜ ነው
አባት ሳለ አጊጥ ተባለውን ቃል
መንፈሴ ተረድቶ ደህና አድርጎ ያውቃል
ደፋሩ፡- ትዝ ይለኝ ጀመረ የዚህ ቀደም ልምዴ
አባባ ሽርሽር አትወስደኝም እንዴ
ዳሞን፡- የለም ተመልሼ አይቀርም መሄዴ
/ሁሉም ተደናግጠዋል/
ታሪኩን ዘርዝሬ ልገልጠው ነው አሁን
ስለዚህ ልባችሁ ድፍረት ያለው ይሁን
አንዴ ከፈሰሰ ውሃ አይታፈስም
መንፈሰ ጠንካራም በከንቱ አያለቅስም
መመለስ ካልቻለ የመጣን አደጋ
ፊት ለፊት የሄዳል ደፋር ሰው ሳይሰጋ
የማይቀር ነውና የሰው ልጅ መሞቱ
ለጨዋነት መስመር አይበልጥም ሕይወቱ
እኔም ሳላስበው ዕድሌ ጠሞብኝ
የማይቀረው ዕዳ ሞት ተፈረደብኝ
/ሁሉም ይደነግጣሉ/

ግን በእናንተ ፍቅር መንፈሴ ታውኮ
ነፍሴ ተሰቃይታ ሃሳቤም ተማርኮ
ለጥቂት ጊዜ እንኳን እረፍትን ስላጣሁ
ፈቃድ ተቀብዬ ልሰናበት መጣሁ
ውድ ጓደኛዬ ከሞት ጋር ተጋፍጦ
ከሕይወቱ በላይ ፍቅርን አብልጦ
በእውነተኛ ስሜት በቆራጥ መንፈሱ
ዋስ ሆነኝ ስለኔ ብቀር ሊሞት እርሱ
ስለዚህ በፍጥነት ጊዜ ሳያልፍብኝ
በቀጠሮ ሰዓት መገኘት አለብኝ
ከዚህ በተረፈ እንዳይቸግራችሁ
ሃብቴ የሚገኝበት ቁልፉ ያውላችሁ
በሉ እንግዲህ ልሂድ እግዚአብሔር ይሁናችሁ

አልማዝ፡- አይ መፈጠር ከንቱ አይ ኑሮ በደል
ልሂድ ይለኝ ጀመር ባሌ ለመገደል
አአልታየኝ አለ ቀኑ ደበዘዘ
ጉልበቶቹ ዛሉ አካሌም ደነዘ
መፈጠሬን ጠላሁ መኖሬም መረረኝ
እንግዲህ በዓለም ላይ ምንድነው የቀረኝ
ብርቱካን፡- በተስፋ ስንኖር በአንተ ላይ ተማምነን
አባብዬ አትሂድ የትም አትበትነን
እባክህ አባባ እኔ አልሄድም በለን
በኦረ ጫካ ላይ ለጅብ አትጣለን
/ታለቅሳለች/
አልማዝ፡- የለም ሲቀልድ ነው አይደለም ከምሩ
የኔ ባል ጨክኖ እንዲህ መናገሩ
/ታለቅሳለች/
ደፋሩ፡- አትሙት አባባ ባንተ ስንመካ
እኔ ልሙት እንጂ ስላንተ ልተካ
ካንተ ተለይተን እስከ መጨረሻ
በድኖች እንሆናለን የለንም መድረሻ
/ያለቅሳሉ/
አልማዝ፡- ዳሞን የእኔ ወንድም የሕይወቴ አለኝታ
ጥቂት ቃል ልንገርህ አድምጠኝ አንድ አፍታ
ማንም አያገኝህ ብንሄድ ርቀን
ቤት ርስታችንን ሃብታችንን ለቀን
ዳሞን፡- /በቆራጥ መንፈስ/
የልም እንዲህ አትበይ
እውነትን መበደል

በጨዋ ሰዎች ዘንድ የሚገባም አይደል
የታሰረው ጓዴ እንደነፍሴ የማምነው
ስለእኔ ሕይወቱን የለወጠልኝ ነው
እንድሞት ተፈርዶ እስር ቤት ብገባ
ጥቂትም ሳይፈራ የኔ ባልደረባ
ኃላፊ ዋስ ሆነኝ እሞት ግዳጅ ድረስ
እኔ እንደምን ልቻል ጥቂትም ሳልሳሳ
ጓደኛዬን መካድ መሆን ለከስካሳ
እንደዚህ ከሚሆን የዚህ ሰው ዋጋው
ይሻል አይደለም ወይ በጩቤ ብወጋው
ተሰቃየሁ እኮ መንፈሴ ደንግጣ
ይህን ልትጠይቂኝ ልብሽ እንዴት ቃጣ
አልችልም ለማረድ ፍቅርን በካራ
ከሞት የበለጠም ቢመጣ መከራ
ራሴን በመውደድ በተንኮል በክፋት
አይቃጣም መንፈሴ ቁም ነገርን ማጥፋት
በሉ ደህና ሁኑ ጊዜያቱ አለፉ
ምንም ቃል የለኝም ከዚህ በተረፈ።

/እየተንሰቀሰቁ ሲያለቅሱ ወጥቶ ይሄዳል/
ትዕይንት 4

ፍርድ ማስፈፀሚያ አደባባይ ፒስያ በዘብ ተይዞ እንደደረሰ ዲዮስዮስ እና ህዝቡ ተሰብስቧል፤ ዲዮንስዮስ ቦታውን ይዞ ተቀምጧል፤ ፒስያ ወደ መገደያው ሲያልፍ

ፒስያ፡- ዲዮንስዮስ ሆይ...
ፍቀድልኝና ልናገር አንድ ቃል
ዲዮንስዮስ፡- አየህ...በሰው ዕዳ መግባት እንዲህ ያስጨንቃል
ሰዓቱ ደረሰ ጓደኛህ አልመጣም
ያንተ ለሱ መሞት ያሳዝናል በጣም
ፒስያ፤- በዚህ አልቆጭም በፊት ፈቅጃለሁ
ለጓደኛዬ ስል ሞተን መርጫለሁ
ሰዓቱ ተላልፏል የተስማማንበት
ምንድነው ጥበቃው ልገደል በፍጥነት
ውድ ጓደኛዬን መንገድ ላይ አደጋ
አግኝቶት ይሆናል በጣም የሚያሰጋ
ይህ ካልሆነ በቀር ጓዴን አምነዋለሁ
በቀጠሮ ፀንቶ እንዲመጣ አውቃለሁ
ግን የቀጠሮአችን ከደረሰ ጊዜው
ቢመጣም ባይመጣም ዕድሉ የእኔ ነው
ስለዚህ ልገደል ቅሬታ አይገባኝም

ከዚህ የበለጠ ደስታ አላገኝም።

ዲዮንስዮስ፡- /በቁጣ/

ይህ አደራረግህ ለተአምር ቢሆንም
ደህ በመግባትህ መሞትህ አይቀርም
ምህረት አላደርግም ለእነዲህ ያለው ጉዳይ
ራስህ ነህ እኮ ራስህን ገዳይ
በሌላው ሰው በደል ወደህ በመግባትህ
ማንም አያዝንልህ አይቀርም መሞትህ
ጊዜ አትስጡት እዚህ ለህዘን ለአቤቱታ
ዘበኞች ውሰዱት እመግደያው ቦታ
መሞቱ እኮ አይቀርም በደልም ባይሰራ
ከድቶት ስለቀረ የእርሱ ባልንጀራ

ዘቦች ፒስያን ወደ መግደያው ቦታ ወስደው እንዳቆሙት ከህዝቡ ግፊያ ዳሞን አሳልፉኝ እያለ ሲወተውት ይታያል።

ዳሞን፡- ልቀቁኝ...ጉዳዩን አልፈ ልናገር
ይህ ሰው እንዳይሞት በማያውቀው ነገር
እሱ ዋሱ እንጂ አጥፊ እንዳይመስላችሁ
ልቀቁኝ ላስረዳ ለእግዚአብሔር ብላችሁ
ጊዜው እኮ ሮጠ በከንቱ አይገደል
ኧረ ችላ አትበሉ የሚገባም አይደል!

/ከብዙ ድካም በኋላ ዘቡ ዳሞንን መምጣት ወደ ዲዮንስዮስ ዘንድ ይቀርብና ያስረዳል.../

ዘበኛ፡- በላብና በደም አቧራ ተነክሮ
የዚያሰው ጓደኛ ከቅድም ጀምሮ
ሥርዓት ለማስከበር እኔ ስከላከል
በኃይል እየጮኸ ከህዝቡ መሃከል
ወንጀለኛ እኔ ነኝ ቀርቤ ላስረዳ
ይህ ሰው ሳያተፋ ከንቱ እንዳይጎዳ
ልቀቀኝ እያለ ስለወተወተኝ
ጨክኜም ተመለስ ማለት ስላቃተኝ
ምን እንደማደርግ ብልሃት ስላጣሁ
ደፍሬ እርስዎ ዘንድ ልነግርለት መጣሁ

/ፒስያ ሊገደል ከቆመበት ቦታ ያሉት ዘቦች ጉዳዩ ጉዳዮ ገርሟቸው ይወያያሉ

ዘብ 1፡- አየህ..እዚያ ማዶ ምንድነው ነገሩ
በጣም አመለጠን በዝቷል ግርግሩ
ዘብ 2፡- ያውልህ ፊትለፊት በላብ የታጠበ
ለምን እንደሁ እንጃ አንድ ሰው ቀረበ
እስኪ ቀረብ ብዬ ተመልክቼ መጣሁ

/ወደ ዲዮንስዮስ አቅራቢያ ለመስማት ይሄዳል/

ፒስያ፡- ጓዴ እንደማይከዳኝ አውቃለሁ መች አጣሁ
ዘበኞች ልገደል እኔ አልፈራም ሞትን
በጓደኛዬ ላይ አይቼ ሕይወትን
ዲዮንስዮስ፡- ይህ ነው እውነተኛ የልብ ባልንጀራ
በል ፈጥነህ ሂድና እስረኛውን ጥራ
/አንድ ዘበኛ ይሄድና ፒስያን ከመግደያው ቦታ ይዞት ይመጣል/
ዳሞን፡- ዲዮንስዮስ ሆይ...
ስመጣ መንገድ ላይ ፈረሱ ሞተብኝ
እስካሁን መዘግየት ግዴታ ሆነብኝ
ነገር ግን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው
ሳይሞት አገኘሁት ጓደኛዬን ይኸው
የአምላክ ፈቃድ ሆኖ ሁለት ጊዜ እንዳልሞት
ለማየት አበቃኝ አለኝታዬን በሕይወት
አሁንም ይልቀቁት ጓዴ እንዳ እንዳይገደል
የምቀጣ እኔነኝ በሰራሁት በደል!
1 ኛ ሹም፡- ይህስ ተአምር ነው ያልተሠራ በዓለም
በህልሜ እንደሁ እንጂ በውኔስ አይደለም
2 ኛ ሹም፡- እንዲህ ያለ ታሪክ ከዚህ አስቀድሞ
አይቼም ሰምቼም አላውቅም ፈፅሞ
ገና አሁን ተረዳሁ የፍቅርን ትርጉም
ለካስ ጓደኝነት እንዲህ አለው ጥቅም
ዳሞን፡- ውድ ምስጢሬ ሆይ የሕይወቴ አለኝታ
እንኳን አተረፈህ የላይኛው ጌታ
በእኔ የተነሳ ስቃይ ፍዳ አይተህል
ወደ ቤትህ ሄደህ ማረፍ ይሻልሀል
...ዲዮንስዮስ ሆይ
ይለቀቅ እንግዲህ ይህ የምሩ ጓዴ
ፒስያ፡- ምን ሆንክ አበድክ እንዴ
የደከምከው አንተ ፀሀይ ያጠቆረህ
ይልቅስ እንድታርፍ ተመለስ እቤትህ
በጣሙን ስጨነቅ በጣሙን ስሰጋ
ያገኘሃል ብዬ ያልታሰበ አደጋ
ፈጣሪ አምላካችን መልክህን አሳየኝ
በል አሁን እረፍ የምሞት እኔ ነኝ!

1 ኛ ሹም፡- ይህ አይደረግም ይገርማል ይደንቃል

ጭሰኛ ባለርስት መቼ ሆኖ ያውቃል

2 ኛ ሹም፡- አየህ ምንም እኮ ጥፋት ሳይኖርበት
አሁንም ፈልጓል ለጓደኛው ሊሞት
ለካ ሞት ቢመጣም አያስደነግጥም
ማናቸውም ነገር ከፍቅር አይበልጥም!
አይተን ስንገረም ዋስ መሆኑን አምኖ
ለጓደኛው ሊሞት ፈለገ ለምኖ

ዳሞን፡- በእኔ ስለሆነ ፍርዱ የተፈረደው
ጓዴ ጣልቃ ገብተህ ባታስቸግር ምነው
ዲዮንስዮስ ሆይ...ይለቀቅ ይህ የምሩ ጓዴ

ዲዮንስዮስ፡- እዚህ ወደ እኔ ዘንድ አስቲ እምጣቸው አንዴ
/ሁለቱም ቀረብ ብለው ይቆማሉ/
እንደናንተ ያለ ሰው ቀድሞም አልገጠመኝ
የአፈጣጠራችሁ ምስጢሩ አልገባኝም
በጣም ልቤን ነካኝ ይህ ቁም ነገራችሁ
እኔንም ጓደኛ አርጉኝ እባካችሁ!
/አጋፋሪውን/
በል አንድ አንድ ሺህ ብር በፍጥነት ስጣቸው
እቤታቸውም ድረስ እንድትሸኛቸው
ከሁሉም ይበልጣል ክቡር ነው ሥራቸው
የበለጠ ዋጋ ለሰው ልጅ በዓለም ላይ
ምንም ነገር የለ ፍቅርን በልጦ የሚታይ
ፍቅር አስተሳሳሪ ኃይለኛ ገመድ ነች
እይዋት ሁሉን በልጣ ድል እንዳደረገች
በሉ ደህና ሁኑ የእኔ ባልንጀሮች!

----------//----------

ወስብሐት ለእግዚአብሔር
ወለወላዲቱ ድንግል
ወለመስቀሉ ክቡር
አሜን!

ተፈጸመ